# አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!
# ኢትዮጵያችን
# ሕዝባዊ ንቅናቄ

## ፕሮግራም

**መስከረም ፰ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም. (September 18, 2016)**

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

© የባለቤትነት መብቱ በሕግ የተጠበቀ

## “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ፕሮግራም

## *መግቢያ*

*ኢትዮጵያ ሀገራችን ባህሏን፣ ሃይማኖቷንና ክብሯን ተገን ያደረገ ሕዝባዊ አንድነት ይጠናከር ዘንድ አማራጭ ይዞ መነሳቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ኢትዮጵያ ሀገራችን በዘርና በሃይማኖት ተከፋፍላና አንድነቷን አጥታ የውጭ መንግሥታት እንዳሻቸው ይገዟት፣ ይቆጣጠሯት ዘንድ ከአሥርተ ዓመታት በፊት ያቀዱት ዛሬ “እየሠመረላቸው” ይታያል። የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋና ዘር ይዛ የግዛት አንድነቷንና ሕዝባዊ ፍቅሯን ጠብቃ የኖረች ጥንታዊ ሀገራችን ዛሬ ሊበታትኗት ዘረኝነትን በመላ ሀገሪቷ ዘርተው ሊያጭዱ ቋምጠዋል። በዘመነ ቅኝ ግዛት ለውጭ ወረራ ኃይል ያልተበገረች አፍሪካዊት ሀገር ዛሬ በልጆቿ ዕኩይ ተግባር ክብርና ማንነቷን እያጣች ነው። አንድነቷ እየሳሳ ነው። ይህች ከዓለም ጥንታዊ የሥልጣኔ ጫፍ በታሪካዊ ቅርሶቿ የተመዘገበች ሀገር ዛሬ እራሷንና ልጆቿን መመገብ አቅቷታል። በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች የነፃነት ተምሳሌት የሆነው ሰንደቅ ዓላማዋ ዛሬ በዘረኝነት መቀስ እየተበጣጠሰ ይገኛል። ሀገሬን ያሉ ብርቅዬ ትውልዶን ያጣችው ሀገራችን “ስደት ለባርነት” እንዲሉ የልጆቿ ዕጣ ሆኖ በመላው ዓለም ተበትነዋል። ኢትዮጵያዊነት ከቶም እንዳያንሰራራ በውጭ ኃይሎችና በውስጥ የሀገር ጡት ነካሾች የተውጠነጠነው ሴራ ዛሬ በሀገራችን ስለ ልማትና ዕድገት ሳይሆን ስለ እልውናዋ እንድናስብ አድርጎናል።*

*“አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትና የሕዝቧን ጥንታዊ ትስሥር ከግምት በማስገባት ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ትጓዝ ዘንድ የንቅናቄውን ፕሮግራም ማውጣት አስፈልጓል። ዛሬ በሀገራችን የተንሰራፋውን የወያኔ ዘረኝነት አገዛዝ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ለመተካት ተነስተናል። በቅኝ ግዛት ወረራ ዘመን ያልተደፈረች ሀገራችን ዛሬ ባዕዳን ኃይሎች እንደ ሸረሪት ድር ወረዋት አንጡራ ሀብቷን የመዝረፋቸው ሂደት እንዲያበቃ “ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን” ብለን ተነስተናል። የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦችን ያቀፈች፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያሏት፣ የተለያዩ አኩሪ ባህል ያላት፣ ጥንታዊ ሀገርነቷን መሥካሪ ታሪካዊ ቅርሶቿ የመሰከሩላት፣ ቀዳሚ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተቀባይ የሆነች ሀገራችን ሁሉንም ልጆቿን በአንድነት አቅፋ ትጓዝ ዘንድ መሪና አታጋይ ፕሮግራም በማስፈለጉ ይህንን አቅርበናል።*

*ሀገራችን የበርካታ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን በግምት በማስገባትና የተነሳውን የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄ የደርግ አገዛዝ በ17 ዓመታት በዘረጋው ጦረኝነት ፖሊሲ መፍትሄ ከማስገኘት ይልቅ ወደ ተባባሰ ችግር ሀገሪቷን ከቶ ሄዷል። በወያኔም የ25 ዓመታት አገዛዝ ኢትዮጵያን አዳክሞና ከፋፍሎ ለመግዛት ከአለው የዘረኝነት ፖሊሲ ጉዳዩን ይብልጥ አወሳስቦ ዛሬ የሀገራችን ህልውና አጠያያቂ መስቀለኛ መንገድ ላይ ዘፍቋታል።*

*በቀጣይነት ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ ይህ መርዘኛ የዘረኝነት አደጋ ተውግዶ ሁሉም በኢትዮጵያዊነቱ ዋናው አጀንዳው ሀገሩን በራሱ ለራሱ ወደ ሥልጣኔና ልማት ጎዳና ታመራ ዘንድ ብሔራዊ የሀገር ፍቅር ስሜት በጉልበትና በጦርነት ሳይሆን ሁሉም አምኖበትና መክሮበት ዳግም ያብብ ዘንድ መደረግ ያለበትን አቅጣጫ ጠቋሚ ፕሮግራም አዘጋጅተናል።*

*በዚህ ፕሮግራም መሠረት ለአለፉት 40 ዓመታት ያልተፈታውን የብሔር/ብሔረሰቦች ችግር በኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ፈትቶ “አንድ ሕዝብ አንድ ሀገር” ለመገንባትና በሂደት የሁሉንም ብሔር/ብሔረሰቦች ባህልና ቋንቋ ተገን በማድረግ የሁለቱን ዋና ዋና እምነቶች (የክርስትናንና*

የእስልምናን) አብሮ የመኖር ጸጋ የተላበሰች ሀገር ለመገንባት ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ያካተተ ለረዥም ላለ ዓመት ሊዘልቅ የሚገባው የጋራ አመራርን ተገን ያደረገ የሽግግር መንግሥት መመሥረት ላይ ትኩረት አድርጎ የወጣ ፕሮግራም ነው። በዚህ ፕሮግራም መሠረት፦

- ሀገሪቷ ወደ ምርጫ ፖለቲካ ከመግባቷ በፊት በርካታ ተቋማትና ኢንስቲትዩሽን ግንባታ ተደርጎ ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ዳግም ለመገንባትና በተለያዩ ዘሮች መካከል በዘረኛው ወያኔ የተሰነቀረውን የጥላቻ መንፈስ ለማስከን፣
- በሂደት በውይይትና በመተማመን የዘር ፖለቲካ ተወግዶ ሁሉም ስለ ሀገሩ ኢትዮጵያ ዘብ ይቆም ዘንድ መሠረት ለመጣል፣
- "አንድ ኢትዮጵያ አንድ ሕዝብ" ብለን እስከተነሳን ድረስ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ባህልንና ቋንቋን በማዳበር የሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ አንድ መሆኑን ለማስረገጥ፣
- የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን ተቀብለን የብሔር/ብሔረሰቦች ክልል ኢትዮጵያ መሆኗን ለማስተማመንና ወያኔ አመጣሹን የዘር ክልል ለማስወገድ፣
- ኢትዮጵያን በመከፋፈል ለማዳከም ዕቅዳቸው የሆነን የውጭ ኃይሎች ሤራና ተንኮል በማጤን ኢትዮጵያ ለልጆቿ በልጆቿ ትሆን ዘንድ መሠረት ለመጣል፣
- ሀገራችን የውጭ ባዕዳን ሸቀጥ ማራገፊያና የሀገራችንን ሀብት ወደ ውጭው አሻጋሪዎች መናኸሪያነቷ አብቅቶ የራሳችንን ባህልና ሃይማኖት ተገን ያደረገ "ሀ" ብለን የምንጀምረው ቅድሚያ ለሀገራችንና ለሕዝባችን የሰጠ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ለመጣልና ወደ ዕድገት ጎዳና ለማምራት፣
- በውጭው ዓለም ተሰደው ያሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዘመናዊ ባርነት ተላቀው ወደ ሀገራቸው ገብተው ያለውን ችግርና መከራ ከሕዝባቸው ጋር ተጋርተው ኢትዮጵያን እንዲያድኗት፣
- የኢትዮጵያንና የሕዝቧን አንድነት በአስጠበቀ መልኩ ሀገራችንን ወደፊት ለማራመድ ሻቢያ ለኢትዮጵያ አንድነት ጸር መሆኑን ተቀብለን በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ ሳናስገባ ከኤርትራ ሕዝብ ጋር ቀና ግንኙነት ለመመስረት፣
- በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ምሁራን፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ መካከል ያለውን መለስተኛ አለመግባባት በውይይትና በመተማመን ለመፍታት፣
- በተለይ በደርግ አገዛዝ በደረሰው አንድ ትውልድ ማጥፋት ቀይ ሽብርና የጅምላ ጭፍጨፋ ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት በሀገራችን ለደረሱት ፖለቲካዊ ችግሮች ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ባስቀመጠ መልኩ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ እንዲደረግ፣ ወዘተ

የተጠናከረ መሠረት ለመጣል ከወያኔ ውድቀት በኋላ የሚመሠረተው የጋራ የሽግግር መንግሥት ቢበዛ ለቀጣይ 10 ዓመት ሀገሪቷን በማስተዳደር መሠረት ይጥል ዘንድ ትኩረት ያደረገ ፕሮግራም ነው።

ይህ የንቅናቄው ፕሮግራም ዋና ዋና የሀገራችን ጉዳዮች ላይ ማለትም፦

- መንግሥታዊ አወቃቀር
- ፖለቲካዊ አሠራር
- የኢኮኖሚ ፖሊሲ
- ዴሞክራሲያዊ መብት
- ማኅበራዊ ጉዳዮች        ትኩረት በመስጠት ተዘጋጅቷል

*አንቀጽ 1 . የንቅናቄው ዓላማ*

1.1. ዘረኛውን የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለመጣልና ሕዝባዊ መሠረት ያለው አገዛዝ በሀገራችን ለማስፈን ሕዝቡን በማስተባበር ለሕዝባዊ ንቅናቄ ለማነሳሳት
1.2. የኢትዮጵያንና የሕዝቧን አንድነት ባስጠበቀ መልኩ ፀረ-ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ ትግሉን ከሌሎች ሕዝባዊ ኃይሎች ጋር በጋራ ለማቀጣጠል
1.3. በዘር የተከፋፈለ ፖለቲካ ቦታውን ለኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ይለቅ ዘንድ መሥራት
1.4. የኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነትና የሕዝቧ ዴሞክራሲያዊ አንድነት በሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎት ላይ በተመሠረተ ሕገ መንግሥት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ መሥራት።

## መንግሥታዊ አወቃቀር

*አንቀጽ 2. የሽግግር መንግሥት*

2.1. ኢትዮጵያ ሀገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግር በጋራ ለመፍታትና ለወደፊቷ ኢትዮጵያ መሠረት ለመጣል የተለያዩ አካላትን ያሳተፈ የሽግግር መንግሥት መመሥረት።
የሽግግር መንግሥቱ፦
- በሀገሪቷ ውስጥም ሆነ ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን
- በብሔር/ብሔረሰብ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን
- የተለያዩ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ወኪሎችን
- የተለያዩ የብዙሃንና የሙያ ድርጅቶች ወኪሎችን (ከመምህራን ማህበር፣ ከሠራተኛው ማህበር፣ ከጋዜጠኛ ማህበራት፣ ከደራሲያን ማህበራት፣ ከተማሪዎች ማህበር፣ ከወጣቶች ማህበር፣ ከሴቶች ማህበር ወዘተ)
- ከአዲስ አበባ ከየከፍተኛውና ቀበሌ የሕዝብ ወኪሎችን
- ከክፍለሀገራት ከአውራጃና ወረዳ የሕዝብ ወኪሎችን
- ከገበሬ ቀበሌ ማኅበራት የአርሶ አደሩ ወኪሎች
- ከክርስትና እና እስልምና ሃይማኖት ተወካዮችን
- ከፖሊስ ሠራዊትና ከጦር ሠራዊት ወኪሎችን
- ምሁራን እና ታዋቂ ግለሰቦችን
- የሀገር ሽማግሌዎችን
- የሕግ ባለሙያዎችን ያካተተ ይሆናል

2.2. የሽግግር መንግስቱ ቢበዛ ለ10 ዓመት ሀገሪቷን ያስተዳድራል።
2.3. የሽግግር መንግሥቱ በሀገራችን የተፈጠረውን የዘር ፖለቲካ በመግባባትና በመወያየት በተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ዘንድና የኅብረተሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም ያብብ ዘንድ መሥራት።
2.4. በዋና ዋና የሀገሪቷ እምነቶች ማለትም በክርስትና (በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክ፣ መሠረተ ክርስቶስ ወዘተ)እና በእስልምና ሃይማኖቶች ዘንድ የተፈጠረውን መለስተኛ ልዩነት በማለዘብና የእምነትንና ሃይማኖትን ነፃነትን በጠበቀ መልኩ ሁለቱም ሃይማኖቶች ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው አንድነት ይተጉ ዘንድ መሠረት መጣል።
2.5. በኢትዮጵያ ህዝብ ንቁ ተሳትፎና ውይይት የሚጸድቅ የሀገሪቷን ሕገ መንግሥት በማርቀቅ ለሕዝበ ውሳኔ ማቅረብ።

2.6. የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግሥትና የክፍለሀገራት አስተዳደርን የሥልጣን እርከን በሚገባ መለየት
2.7. የተለያዩ የብሔር/ብሔረሰብ ወይም የዘር ፖለቲካ ድርጅቶች በውይይትና በሂደት በመክሰም ብሔራዊ አጀንዳ የያዙ ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ድርጅቶች የሚጠናከሩበትን ሂደት ማመቻቸት።
2.8. ዘርን ተገን ያላደረገ የኢትዮጵያ ግዛት አከላለል በተፈጥሮአዊ የሀገሪቷ አቀማመጥ መተካት።
2.9. ተመሳሳይ የፖለቲካ ፕሮግራምና አጀንዳ ያላቸው ሕብረ ብሔር ድርጅቶች በፈቃደኝነትና በመግባባት እየተዋሃዱ የተወሰኑ ፖለቲካ ድርጅቶች ነጥረው እንዲወጡ ጥረት ማድረግ።
2.10. በግብርናውም ሆነ በኢንደስትሪ መስክ የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ፖሊሲ መቅረጽ
2.11. በሀገሪቷ የዴሞክራሲያ ባህል ይዳብር ዘንድ ከሽግግር መንግሥቱ በቀጣይነት የምርጫ ፖለቲካ ጽንሰ ሀሳብ በሚገባ ይዳብር ዘንድ አስፈላጊውን ተቋማት ግንባታ ማድረግ
2.12. ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት መሠረት ያደረገ የጦር ኃይልና የፖሊስ ሠራዊት መገንባት

### አንቀጽ 3. ሕገ መንግሥት

3.1. ሕገ መንግሥቱ በሽግግር መንግሥቱ አማካይነት ረቂቁ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይቀርባል
3.2. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በነፃና በግልጽ ውይይት በሕዝበ ውሳኔ ይጸድቃል
3.3. ሕገ መንግሥቱ በሀገሪቷ ማዕከላዊ መንግሥትና በተዋረድ ባሉ ክፍላተ ሀገራት መካከል ያለውን የሥልጣን ዕርከን በግልጽ ያስቀምጣል
3.4. ሕገ መንግሥቱ በምርጫ ሥልጣን ለሚይዘው የፖለቲካ ፓርቲ የሥልጣን ዘመንና ኃላፊነት በሚገባ ያስቀምጣል
3.5. የመንግሥት ሥልጣን አደረጃጀትና አወቃቀርን ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በአማከለ መልኩ በግልጽ ይቀመጣል
3.6. በሕገ መንግሥቱ የሕግ አውጪው፣ የሕግ አስፈፃሚውና የሕግ ተርጓሚው አወቃቀር፣ ሥልጣንና ኃላፊነታቸው በግልጽ ይቀመጣል

### አንቀጽ 4. የፖለቲካ ፓርቲዎች

4.1. በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.7 መሠረት ዘርንና ሃይማኖትን ተገን ያደረገ ፖለቲካ ድርጅት አለመፍቀድ።
4.2. ኅብረ ብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች በየትኛውም የሀገሪቷ ክልል መንቀሳቀስና ጽ/ቤት መክፈት መብታቸውን ማወቅ
4.3. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ሕዝብን የማደራጀት የመቀስቀስ መብቱን ማወቅ
4.4. በማንኛውም ጊዜ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን ሕብረ ብሔር የፖለቲካ ድርጅት የማቋቋም መብት መፍቀድ
4.5. በሕዝብ ምርጫ የተሸነፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሥልጣን ለያዘው አካልና ለቀጣዩ የሀገሪቷ ምክር ቤት ተባባሪና አጋር ይሆናሉ

### አንቀጽ 5. የኢትዮጵያ ግዛት አከላለል

5.1. የኢትዮጵያ የግዛት አከላለል
 5.1.1. የሀገሪቷን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ መሠረት ያደርጋል
 5.1.2. ወይም በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበረውን የክፍለሀገራት አስተዳደር ይይዛል

5.2. በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.8 መሠረት ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር በመሆኗ ዘርን ተገን ያደረገ የግዛት አከላለል በአዲሲቷ ኢትይጵያ ቦታ አይኖረውም።
5.3. እያንዳንዱ ክፍለሀገር የራሱ አውቶነመስ አስተዳደር ይኖረዋል
5.4. ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በፈለገው የሀገሪቷ ክልል የመዘዋወር፣ የመኖር፣ የመሥራት መብቱ የተጠበቀ ነው

### አንቀጽ 6. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

6.1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በላዩ ላይ ምንም ተጨማሪ የሌለበትና በአግድሞሽ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማትን ይይዛል።

### አንቀጽ 7. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ

7.1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል።
7.2. የኢትዮጵያን የተለያዩ ቋንቋዎች ባለቤትነቷን ከግምት በማስገባት የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የሚዳብሩበትና የሚያድጉበትን መሠረት መጣል።

## የዴሞክራሲያና ሰብአዊ መብት

### አንቀጽ 8. ፍርድ ቤት

8.1. ማንኛውም ፍርድ ቤቶች ከመንግሥትና ፖለቲካ ድርጅቶች ነፃ ሁነው ይቋቋማሉ
8.2. ማንም ግለሰብ ካለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር አይደረግም/አትደረግም
8.3. ካለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የማንም መኖሪያ ቤት፣ ድርጅት አይፈተሽም
8.4. ፖሊስ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማንንም ዜጋ ከ24 ሰዓት በላይ በቁጥጥር ሥር ማዋል አይችልም

### አንቀጽ 9. የብሔር/ብሔረሰቦች መብት

9.1. ሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች የትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ሀገራቸው ነው።
9.2. የብሔር/ብሔረሰቦች መብት ከመገንጠል ባሻገር ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው።
9.3. ብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ እምነታቸውን፣ ታሪካቸውን የማዳበርና የመጠበቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው።
9.4. ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰብ እኩል መብት አላቸው

### አንቀጽ 10. ሃይማኖት

10.1. በኢትዮጵያ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል ናቸው።
10.2. የክርስትናና የእስልምና እንዲሁም ለሎች ሃይማኖቶች ለኢትዮጵያ ሀገራቸው አንድነትና ለሕዝባቸው ደህንነት የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ጥረት ኢትዮጵያ ትቀበላለች።
10.3. መንግሥት የእምነት ቦታዎችና ቅርሶች እንክብካቤና ደህንነት ትኩረት ይሰጣል።
10.4. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የእምነት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው።
10.5. መንግሥት በክርስትና ሃይማኖት ሲኖዶስ እና በእስልምና ሃይማኖት መጅሊስ አመራረጥም ሆነ አሠራር ላይ ጣልቃ አይገባም

10.6. በሀገር ቤትና በውጭው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ተቋማት በጋራና በአንድ መማክርት ይሠሩ ዘንድ ማመቻቸት

### *አንቀጽ 11. ዴሞክራሲያዊ መብት*

11.1. በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የግለሰብም ሆነ የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብት ለሁሉም ያለገደብ ይከበራል።

11.2. በኢትዮጵያ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ለሁሉም ዜጋ ይከበራል።

11.3. ሕዝቡ ለሚያነሳው ጥያቄ ተማሪዎች ትምህርት በማቆም፣ ሠራተኞች ሥራ በማቆም ድጋፋቸውን የመስጠት መብታቸውን ማወቅ

11.4. አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.1. እንደተጠበቀ የመደራጀት መብትን ማክበር

11.5. በማንኛውም የሀገሪቷ ክልል የመዘዋወር፣ የመማር፣ የመሥራትም ሆነ የመኖር መብትን ማረጋገጥ

11.6. የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን ስርጭቶችን መፍቀድ

11.7. የሶሻል ሚድያዎች ፌስ ቡክ፣ ቲውተር፣ ድረ ገጽ ግንኙነቶችን መልቀቅ

11.8. የሞባይል ስልኮች፣ ቫይቨር፣ ስካይፒ፣ ፓልቶክ እና ሌሎችን የመገናኛ አውታሮችን በነፃነት የመጠቀም ባህልን ማዳበር

### *አንቀጽ 12. የሴቶች መብት*

12.1. የሴቶች ከወንዶች እኩል መብት ማረጋገጥ

12.2. ሴቶች በፆታቸው የመደራጀት መብታቸውን ማክበር

12.3. ከ18 ዓመት በታች ያሉ ሴቶች እንዳያገቡ በሕግ ማገድ

12.4. ለሴቶች የትምህርት ዕድል ማግኘት አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት

12.5. ሴቶች በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት በቂ የእረፍት ጊዜ መስጠት

12.6. በሴቶች እና በሕፃናት ላይ የሚደርሰውን አስገድዶ መድፈር ሙሉ በሙሉ ማስቆም

12.7. ሴተኛ አዳሪነትን ለማስቀረት መንስሄዎቹን አጥንቶ መፍትሄ ለመስጠት መጣር

### *አንቀጽ 13. የሠራተኛው መብት*

13.1. የሠራተኛው የሳምንት የሥራ ሰዓት 40 ነው።

13.2. የሠራተኛውን ነፃ የመደራጀት መብት ማረጋገጥ

13.3. የሠራተኛውን አነስተኛ ደመወዝ ከሀገሪቷ የኑሮ ደረጃ አንፃር መወሰን

13.4. ሠራተኛው እንደገቢው መጠን በተመጣጣኝ ክፍያ ወይም በነፃ ሕክምና የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት

13.5. የሠራተኛውን የሥራ ጥራት ለመጠበቅ በተለያዩ የሙያ ዘርፍ ላሉ ሠራተኞች አጫጭር ስልጠናዎች ያገኙ ዘንድ ማመቻቸት

13.6. ለሠራተኞች ከወር ደሞዛቸው በተጨማሪ ለሥራቸው አስፈላጊውን የአልባሳትና የቁሳቁስ ድጎማ ማድረግ

13.7. በየዓመቱ ለምስጉን ሠራተኞች አስፈላጊውን ማበርታቻ በማድረግ እውቅና መስጠት

### አንቀጽ 14. የመምህራን መብት

14.1. የመምህራን ማህበርን በነፃ የመደራጀት መብት ማረጋገጥ
14.2. የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ መምህራንን በሙያቸው ዘርፍ አጫጭር ስልጠናዎች ያገኙ ዘንድ ማመቻቸት
14.3. ለመምህራን ከወር ደሞዛቸው በተጨማሪ የአልባሳትና የቁሳቁስ ድጎማ ማድረግ

## <u>ማኅበራዊ መስክ</u>

### አንቀጽ 15. በትምህርት መስክ

15.1. የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግን የትምህርት ፖሊሲ በመሠረዝ ለአብዛኛው ሕዝብ ጠቀሜታ ያለው የትምህርት ፖሊሲ መቅረጽ
15.2. የነፃ ትምህርት ዕድል ይስፋፉ ዘንድ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ
15.3. በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ትምህርት ይስፋፉ ዘንድ የውጭ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ትኩረት ማድረግ
15.4. በከተማ በከፍተኛ ደረጃ በገጠሮች በወረዳ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ 12ኛ ይከፈቱ ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
15.5. የሕፃናት መዋያ ትምህርት ቤቶች በየቀበሌው ይስፋፉ ዘንድ እገዛ ማድረግ
15.6. የትምህርት አሰጣጥ ጥረትን ለማጎልበት አስፈላጊውን የመጽሐፍትና ቁሳቁስ አቅርቦት ማሟላት
15.7. ተማሪዎች የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ እንዲለብሱ ማድረግ
15.8. በዩንቨርስቲና በኮሌጅ ደረጃ እንዲሁም የተለያዩ የምርምር ተቋማት ይስፋፉ ዘንድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ
15.9. በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡትን የማበረታቻ ሽልማት በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ማድረግ
15.10. በየትምህርት ቤቶች የስፖርት፣ የሥነ ጽሁፍ፣ የሥዕል፣ የኪነት ወዘተ ውድድሮች ይካሄዱ ዘንድ ማበረታታት
15.11. የተማሪዎችን ጠቅላላ ዕውቀት ለማዳበር በ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ እንዲሁም በኮለጆችና ዩንቨርስቲ ደረጃ የ«ጠቅላላ ዕውቀት» ውድድሮችን ማካሄድ
15.12. የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶችንና የተለያዩ ባህሎችንና አኗኗሮችን በተለይ በገጠራቱ ኢትዮጵያ ለማስተዋወቅ በተለያየ ቦታና ጊዜ የተማሪዎች «ሀገርህን እወቅ» የሽርሽር ዝግጅት ማድረግ

### አንቀጽ 16. በጤና/ሕክምና መስክ

16.1. ለችግረኞች፣ ለሕፃናትና፣ ለአዛውንት የነፃ ሕክምና ይስፋፉ ዘንድ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ
16.2. መለስተኛ የሕክምና ክሊንኮች በየአካባቢው ይቋቋሙ ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
16.3. የሆስፒታሎችንና የሕክምና ቦታዎችን አስፈላጊ ቁሳቁሶች በተገቢው መጠን ማሟላት
16.4. የህክምና ባለሙያዎችን ጥራትና ብቃት ለመጠበቅ አስፈላጊውን እገዛና የሙያ ሥልጠና ሳያቋርጡ እንዲያገኙ ማድረግ
16.5. መንግስታዊ ያልሆኑ በጎ አድራጊ ተቋማት በሕክምና መስክ ለሚደረጉ ጥረቶች እገዛ ይሠጡ ዘንድ ማመቻቸት

16.6. በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋና በተለያየ ምክንያት ለሚከሰቱ ወረርሽኝ ቅድሚያ ዝግጅት በማድረ አጣዳፊ ዕርዳታ መስጠት
16.7. ለወባ፣ ኤድስ፣ ኢቦላ ወዘተ መሰል በሽታዎች አስፈላጊውን መከላከልና እንክብካቤ ማድረግ

### አንቀጽ 17. በስፖርት መስክ

17.1. ስፖርት ለጤንነት፣ ለወዳጅነት መርህን የተከተለ እንቅስቃሴ ማስፋፋት
17.2. የሀገራችንን ስፖርት ለማዳበር የስፖርትና መዝናኛ ቦታዎችን በየአካባቢው ማቋቋም
17.3. የስፖርት ውድድሮችን በቀበሌ፣ ወረዳ፣ አውራጃና ክፍለሀገር ደረጃ በየዓመቱ ማካሄድ
17.4. የስፖርት ውድድሮችን በትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆችና ዩንቨርስቲ ደረጃ በየዓመቱ ማካሄድ
17.5. በማንኛውም አካባቢ በሚመሠረቱ መንደሮች ለእስፖርትና መዝናኛ ቦታዎች ማዘጋጀት

### አንቀጽ 18. በባህል መስክ

18.1. የብሔር/ብሔረሰቦችን ባህል፣ አኗኗርና ቋንቋ ለመጠበቅና ለማሳደግ የ«ብሔር/ብሔረሰቦች ተቋም» ማቋቋም፣ የቋንቋ ጥናት አካዳሚን ማስፋፋት
18.2. የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦችን ባህል ለማጉልበትና ለማዳበር የብሔር/ብሔረሰቦችን ቀን በተጠናከረ መልኩ በብሔራዊ ደረጃ ማክበር
18.3. በየትምህርት ቤቶች በአመቺው ወቅት የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች የራሳቸውን ባህል የሚያዘጋጁበትን መድረክ ማዘጋጀት
18.4. የብሔር/ብሔረሰቦችን ቋንቋና ባህል ለማዳበር በኪነትና በሥነጽሁፍ ዘርፍ የሬድዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የጋዜጣና፣ መጽሔት ወዘተ ዝግጅቶች ይስፋፉ ዘንድ ጥረት ማድረግ
18.5. ለኢትዮጵያ ባህልና ታሪካዊ ቅርሶች አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ
18.6. በተለያየ ጊዜ በተለያየ መንገድ ከሀገራችን የወጡ ቅርሶችን ለማስመለስ ጥረት ማድረግ

### አንቀጽ 19. ሕፃናትን በተመለከተ

19.1. ሕፃናትን በሕገ ወጥ መንገድ ለውጭ ዜጎች መስጠትን ማስቆም
19.2. በማደጎ ስም ከሀገር የወጡ ሕፃናትን ሁኔታ መከታተል
19.3. ሕፃናትን ለከባድ ሥራ ያለ ዕድሜአቸው እንዳይቀጠሩ ማገድ
19.4. ሕፃናት ላይ የሚደርስ ድብደባ በጥብቅ እርምጃ ማስቆም
19.5. ሕፃናትን አስገድዶ መድፈር፣ ለልመናና ለሴተኛ አዳሪነት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን በሕግ ማገድ
19.6. ለሕፃናት መዋያና መዝናኛ መንግሥት አስፈላጊውን ድጎማ ማድረግ

### አንቀጽ 20. ወጣቶችን በተመለከተ

20.1. የነገው ሀገር ተረካቢ ወጣቶች ብቁ ዜጋ ሆነው ያድጉ ዘንድ በትምህርት መስክ ከፍተኛውን ትኩረት መስጠት
20.2. አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት ወጣቶች በተለያየ ዘርፍ እራሳቸውን እንዲችሉ ማበረታታት
20.3. ወጣቶች ከአልባሌ ሱስና ባህል ተላቀው የነገዋ ኢትዮጵያ ተስፋ ይሆኑ ዘንድ ማስተማር፣ መንከባከብ

20.4. ወጣቶች እርስ በርስ በመንደርና በአካባቢ በጥቅሉ በሚደን የሚያደርጉትን ድብደባ፣ ዝርፊያ፣ አካባቢን ማወክ የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ሆን ብሎ የፈጠረባቸው አደጋ መሆኑን ተገንዝበው ያቆሙ ዘንድ ጥረት ማድረግ

20.5. ብቁ ዜጋ ለማፍራት ለወጣቶች በየአካባቢው በስፖርት፣ በባህል፣ በኪነትና ሌላም መዝናኛ ቦታዎችን ማዘጋጀት

### *አንቀጽ 21. ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ*

21.1. ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት በተለያየ የሙያ ዘርፍ ተመርቀው ሥራ ያላገኙ ምሩቃንን የሥራ ዕድል የሚያገኙበትን ዕቅድ መዘርጋት

21.2. በወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከ10ኛ እና ከ12ኛ ክፍል ትምህርታቸው ሳይቀጥሉ ያለ ሥራ የተቀመጡ ወጣቶችን አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎች እያገኙና ወደ ሥራ ዓለም የሚሰማሩበትን ዘዴ መፍጠር

21.3. በየአካባቢውና በየሠፈሩ ከሥራ ማጣት የተነሳ ለአልባሌ ውሎ የተዳረጉ ወጣቶችን እንደችሎታቸውና እንደአቅማቸው ሥራና ሥልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት

## ***<u>ምጣኔ ሀብት</u>***

### *አንቀጽ 22. ምጣኔ ሀብትን በተመለከተ*

22.1. የአብዛኛውን ሕዝብ ጥቅም መሠረት ያደረገ የሀገር ልማትና ዕድገት ላይ ትኩረት ያደረገ ብሔራዊ ምጣኔ ሀብት ግንባታ ማካሄድ

22.2. ቅጥ ያጣ ብዝበዛና የውጭ ኃይሎችን ዘረፋ ለመቋቋም የልማት ዕቅዳችንን በሀገራችን ሕዝብና በራሳችን ተፈጥሮአዊ ሀብት ለመገንባት ትኩረት መስጠት

22.3. እጅግ ኋላ ቀር ለሆኑ አካባቢዎች ትኩረት የሰጠ የኢኮኖሚ ግንባታ ማካሄድ

22.4. የመንግሥት ተሳትፎ ያካተተ የዕድገትና የልማት መሠረት መጣል

22.5. ለሀገር በቀል ባለ ሀብቶች ቅድሚያ የሰጠ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት

22.6. መንግስት ኢኮኖሚ ተቋማትና ንብረቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች አይሆኑም

22.7. የመንግሥት ኢኮኖሚ አውታሮች ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍል በተውጣጡ ነፃ የቦርድ አካላት ይመራሉ

22.8. መንግሥት በዋጋ ቁጥጥርና ተመን እንዳስፈላጊነቱ ጣልቃ ሊገባ ይችላል

### *አንቀጽ 23. በግብርና መስክ*

23.1. አርሶ አደሮች በሚያርሱት መሬት ላይ ሙሉ በሙሉ የባለቤትነት መብት ይኖራቸዋል

23.2. አርሶ አደሮች በግል ሀብትነት ሊይዙ የሚችሉትን ከፍተኛ የመሬት ሄክታር መጠን መወሰን

23.3. አርሶ አደሮች የኢትዮጵያን ነባር የእህል ዝርያዎች ላይ ትኩረት የሰጠ እርሻ ያካሂዱ ዘንድ ማገዝ

23.4. አርሶ አደሮች ከእርሻ ጎን ለጎን የጓሮ አትክልትና የከብት እርባታዎችን እንዲያካሂዱ እገዛ ማድረግ

23.5. የዝናብ እጥረትንና የተፈጥሮን አደጋ ለመቋቋም ወንዞች በሚያልፉባቸው ገጠሮች በመንግሥት ጭምር የታገዘ ሰፋፊ የመስኖ እርሻ ማካሄድ

23.6. የመጠጥ ውኃ እጥረትን ለመቋቋም የከርሰ ምድር ውኃ ጥናት በባለሙያ እያካሄዱ የጉድጓድ ውኃዎችን በየገጠሩ ቀበሌ ማስፋፋት

23.7. ባለሀብቶች ወይም መንግሥት በመጠነኛ ክፍያ በአንድ አካባቢ ላሉ አርሶ አደሮች ትራክተሮችንና የእርሻ መሳሪያዎችን በማቅረብ ወደ ዘመናዊ እርሻ የሚሸጋገሩበትን መንገድ መቀየስ

23.8. አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን በፈለጉት ቦታና ጊዜ የመሸጥ መብታቸው የተጠበቀ ነው

23.9. መሬት አልባ ለሆኑ አርሶ አደሮችና አዲስ ጎጆ ለሚመሰርቱ አርሶ አደሮች ሊያገኙ የሚችሉትን የመሬት መጠን ማመቻቸት

23.10. በዕድሜ መግፋት፣ በአካል ጉዳት እና በመሳሰሉት አቅም ለሌላቸው አርሶ አደሮች በመንግሥት ትብብር አካባቢው ይዞታቸውን እንዲከባከቡላቸው ማድረግ

23.11. የእርሻ መሬትን እጥረት ለመቋቋም አርሶ አደሮች ወደ አነስተኛ እንዱስትሪ የሚያድጉበትን መንገድ መቀየስ

23.12. በአርሶ አደሮች አካባቢ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ መንገዶች፣ መዝናኛ ቦታዎች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት

### *አንቀጽ 24. በኢንዱስትሪው መስክ*

24.1. ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪው መስክ ልታድግ የምትችልበትን ሁኔታ ትኩረት በመስጠት ማስፋፋት

24.2. ከፖለቲካ ድርጅቶች ነፃ የሆነ የሕዝብና የመንግሥት ተሳትፎ ያለበት የእንዱስትሪ ግንባታ ማካሄድ

24.3. የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በእንዱስትሪው መስክ እንዲሳተፉ አስፈላጊውን እገዛና ትብብር ማድረግ

24.4. የጥሬ ዕቃ አቅርቦት በሚገኝባቸው ተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ተመሳሳይ የእንዱስትሪ ግንባታ ማስፋፋት

24.5. ለቀላልም ሆነ ለከባድ እንዱስትሪዎች ያልተቋረጠ የኃይል ምንጭ (ኤሌክትሪክ) አቅርቦት መዘርጋት

24.6. በእንዱስትሪ አካባቢዎች የትምህርት ቤት፣ የክሊንኮች፣ የመንገድና ውኃ አቅርቦት ግንባታዎችን በሚገባ ማካሄድ

24.7. የውጭ ባለ ሀብቶች እንዱስትሪ ግንባታ በሊዝ መስጠትና በኢንዱስትሪው ሠራተኞች ኢትዮጵያውያን እንዲሆኑ መስማማት

### *አንቀጽ 25. ቅይጠ ሕይወታት አስመልክቶ*

25.1. ኢትዮጵያ የዓለም ኩባንያዎችን የተዳቀሉ ምርት ዘሮች ወደ ሀገር ይገቡ ዘንድ ያደረገችውን ውል መሠረዝ

25.2. ለእርሻ ምርቶች በማዳበሪያ ስም የሚገቡ ዘር አምካኝ መድሃኒቶችን በባለሙያ ተጠንተውና ደህንነታቸው ተረጋግጦ ለአገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ

25.3. በእርዳታ መልክ የሚገቡ ጥራ ጥሬዎች በምንም መልኩ ለዘር ምርትነት እንዳይውሉ ማድረግ

25.4. ኢትዮጵያ በተለያዩ ኩባንያዎች የተወሰደባትን የምርት ባለቤትነት (ለምሳሌ በጤፍ፣ በቡናና በሌሎችም) ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማስመለስ

25.5. የሀገሪቷን ነባር ሰብሎች የሚያቀጭጩና የአፈርን ተፈጥሮአዊ ሂደት የሚሸረሽሩ ምርቶችን ማስቆም (አበባ እርሻ)

### *አንቀጽ 26. ንግድን በተመለከተ*

26.1. የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ምርቶች በቅድሚያ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማዋል
26.2. ለውጭ ንግድ የሚሆኑ ምርቶችን ጥራት በጠበቀ መልኩ ማሳደግ
26.3. የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ከውጭው ዓለም ወደ ሀገራችን የመግባታቸውን መጠን መቀነስ ወይም ማቆም
26.4. ወደ ሀገር በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ተገቢውን ቀረጥ ማድረግ
26.5. ሕገ ወጥ ንግድን ለማስወገድ አስፈላጊውን እርምጃና ማስተካከል ማድረግ
26.6. ከውጭ ኩባንያዎች ጋር የተደረጉ የሀገሪቷን የምርት ባለቤትነት የሚፃረሩ ውሎችን መሠረዝ

### *አንቀጽ 27. በሊዝ የተሰጡ ቦታዎች*

27.1. ለውጭ ኩባንያዎችና ግለሰቦች ያለአግባብ በሊዝ ስም የተሰጡ ባዶ ቦታዎችን ማስመለስ ውሎቹንም መሠረዝ
27.2. በሊዝ ስም ተሸጠው የተጨፈጨፉ የደን ሀብቶችን መልሶ መገንባት
27.3. ለውጭ ኩባንያዎች የተሰጡ የግንባታም ሆነ ማንኛውም ኮንትራት ውሎች መመርመርና ሙሉ በሙሉ በሀገር ባለሀብቶች እንዲያዙ ማድረግ

### *አንቀጽ 28. ትርፍ አልባ በጎ አድራጎት ድርጅቶች*

28.1. ለተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ
28.2. ትርፍ አልባ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ ማመቻቸት

### *አንቀጽ 29. ደንና የተፈጥሮ ሀብት*

29.1. የደንና የተፈጥሮ እንክብካቤን በሚገባ ማጠናከር
29.2. በከተሞች የዛፍ፣ ጽድና የመሳሰሉ ተክሎች ግንባታ ወቅቱን ጠብቆ ማካሄድ
29.3. በገጠሮች የተክሎችና የደን ጥበቃዎችን በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ
29.4. በተለያየ ምክንያት ለሚደርስ የደን ቃጠሎ አፋጣኝ እርምጃና ክትትል ማድረግ
29.5. የዱር አራዊት ቅርሶቻችን የሚዳብሩበትንና የሚጠበቁበትን አቅጣጫ መቀየስ

### *አንቀጽ 30. አካባቢ ጥበቃ በሚመለከት*

30.1. በከተሞች የቆሻሻ ማከማቻዎች በመንደር ደረጃ በሚገባ ማስቀመጥ
30.2. የከተማ ልማት በየአካባቢው የሕዝብ መጸዳጃ ሥፍራዎች ይበራከቱ ዘንድ እገዛ ማድረግ
30.3. በየሆቴል ቤቶች፣ ቡና ቤትና የመሳሰሉት ያሉትን መጸዳጃ ቤቶች ደረጃቸውን ይጠብቁ ዘንድ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ
30.4. ወደ ወንዞች የሚገቡ የመጸዳጃ ቤቶችን ፍሳሽ፣ የፋብሪካ ዝቃጮችን፣ የሚጣሉ ቆሻሻዎችን ሙሉ በሙሉ ማስቆም
30.5. በመንገድ ላይ የሚደረጉ መጸዳዳቶች ይቆሙ ዘንድ በየአካባቢው ለኅብረተሰቡ ትምህርት መስጠት
30.6. በባለሙያዎች በታገዘ መልኩ በተወሰኑ አካባቢዎች የቆሻሻ ማከማቻ ሥፍራ ማዘጋጀት

30.7. ወጣቶች አካባቢያቸውን በተለያዩ ተክሎች በማስዋብ የአካባቢ ጽዳትን ይንከባከቡ ዘንድ እገዛና ትብብር ማድረግ

## *አንቀጽ 31. የትራንስፖርትና መገናኛን በሚመለከት*

31.1. የመንገድ ግንባታዎች በከተማዎችና በገጠሮች ማካሄድ
31.2. አቅም በሚፈቅደው መጠን የባቡር ሐዲዶችን በከተሞችና በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መዘርጋት
31.3. የከተሞችን ትራንስፖርት አቅርቦት ለመቅረፍ የከተማ አውቶቡሶች፣ ታክሲ፣ እና ሌሎችን አቅርቦት ማበራከት
31.4. የክፍለ ሀገር አውቶቡሶችንና የዕቃ ማጓጓዣ እጥረቶችን ለመቅረፍ መጣር
31.5. የአየር ትራንስፖርት በሀገር ውስጥም ሆነ ድንበር ዘለል ጉዞዎችን በሚገባ ማጠናከር
31.6. የነዳጅ አቅርቦትን በተመጣጠነ ዋጋና ያለ እጥረት ማቅረብ
31.7. የቤት ስልክና የሞባይል አገልግሎትን ጥራቱን ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ ጥረት ማድረግ
31.8. የኢንተርኔት አገልግሎት በሰፊው መዘርጋት
31.9. የተቀላጠፈ የፖስታ አገልግሎት መዘርጋት
31.10. በየጊዜው የሚከሰቱ የመኪና አደጋዎችን ለመቅረፍ የአሽከርካሪዎች ደንብና ሕግ በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውልበትን ዘዴ መቀየስ

## *አንቀጽ 32. የኃይል ማመንጫ*

32.1. በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍል ያሉ የኃይል ማመንጫዎችን ማጠናከር
32.2. የዐባይን ጅምር የኃይል ምንጭ ግንባታ ትኩረት በመስጠት ማጠናቀቅ
32.3. አዳዲስ የኃይል ምንጭ ግንባታዎችን ማካሄድ
32.4. የእንፋሎት ኃይል ግንባታን ማጠናከር
32.5. በየትኛውም የሀገሪቷ ክልል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ማጠናከር
32.6. ለፋብሪካዎች፣ ለሕክምና ተቋማትና ለተለያዩ መሥሪያቤቶች ተገቢውንና ያልተቋረጠ የኃይል ምንጭ ማቅረብ
32.7. የተለያዩ ኃይል ምንጭን ለማዳበር (የፀሀይ፣ የንፋስ ወዘተ) ከፍተኛ የምርምርና ጥናት ተቋም መዘርጋት

## *አንቀጽ 33. የባንክና መድህን ኢንሹራንስ ኢንሹራንስ*

33.1. ብሔራዊ ባንክ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ
33.2. የሀገር ባለሀብቶች በንግድ ባንክና በኢንሹራንስ ድርጅቶች ላይ እንዲሠማሩ ማበረታታት

## *አንቀጽ 34. የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት*

34.1. ማንኛውም ሰው የከተማ ቦታና ቤት በግል ንብረትነት መያዝ ይችላል
34.2. ቤት መሥራት፣ ማከራየት፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማውረስ፣ በወለድ አግድ ማስያዝ ይቻላል
34.3. መንግሥት የቁጠባ ቤቶችን በመሥራት የቤት ኪራይ እጥረትን ለመቅረፍ ጥረት ያደርጋል
34.4. ባለሀብቶች ለኪራይ፣ ለንግድ የሚሆኑ የቤትና የሕንፃ ግንባታዎች ላይ እንዲሳተፉ ማገዝ
34.5. በደርግ የተወረሱ ትርፍ ቤቶች በአጥኚ ኮሚቴ ታይቶ ቤቱ የሚመለስበት ወይም ቤቱ ፈርሶ ከሆነ ለባለንብረቱ ካሳ የሚከፈልበት ሁኔታ ይታያል

34.6. በወያኔ ማፈናቀል የግል ቤታቸውን ያለአግባብ የተነጠቁ ቤታቸው ይመለሳል ወይም ተገቢውን ካሣ እንዲያገኙ ይደረጋል

### *አንቀጽ 35. ሙስናና ጉቦኝነት*

35.1. በሀገሪቷ ተንሰራፍቶ ያለውን ሙስናና ጉቦኝነት ለማጥፋት ከፍተኛውን ጥረት ማድረግ
35.2. በሕዝብና መንግሥት ሀብት ዘረፋ የተሠሩ ቤቶች፣ ሕንፃዎች እና ሌሎች በተጠና መልኩ የመንግሥት ንብረት ማድረግ
35.3. ወደ ውጭ ሀገር የወጡ የሀገር ሀብትና ንብረት የሚመለስበትን ዘዴ መቀየስ
35.4. በዝርፊያ ወደ ውጭ ሀገር ባንኮች የገቡ የሕዝብ ገንዘብ የሚመለስበትን ዘዴ መቀየስ
35.5. ጉቦኝነት ሙሉ በሙሉ ይወገድ ዘንድ የሚያስፈልገውን እርምጃ መውሰድ

## <u>የትግል ስልት</u>

### *አንቀጽ 36. የትግል ስልት*

36.1. “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” የትግል ስልት ማንኛውንም መንገድን የተከተለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ማነሳሳት ይሆናል
36.2. ትኩረቱን ሀገር ቤት አድርጎ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳተፈ ፀረ-ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ትግል በመላ ሀገሪቷ ይፋፋም ዘንድ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል
36.3. ዛሬ የሀገራችን ህልውና እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዕድሜ፣ በዘርና በሃማኖት ሳይገድበው የእንቃስቃሴው አካል ማድረግ

## <u>የውጭ ፖሊሲ</u>

### *አንቀጽ 37. የኤርትራ ጥያቄ*

37.1. የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ለኤርትራ እንደ ሀገር እውቅና አለመስጠት
37.2. የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራን እንደ ሀገር ከተቀበለ ከኤርትራ ጋር በኢኮኖሚም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች መልካም ግንኙነት ለመመሥረት በቅድሚያ ኤርትራ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሰብን ለኢትዮጵያ መመለስ ይኖርባታል
37.3. የኤርትራው ሻቢያና የኢትዮጵያው ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያ ሕዝብና አንድነት ፀር መሆናቸውን መቀበል

### *አንቀጽ 38. የውጭ ፖሊሲ*

38.1. በገለልተኝነት መርሆ ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነቶችን ማካሄድ
38.2. የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ለማንም የውጭ ኃይል የወታደራዊ አገልግሎት አይውልም
38.3. ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የፈረመቻቸውን ውሎች (በሰብዓዊ መብት፣ በአየር ብክላ፣ በአሸባሪነት ወዘተ) ማክበር

### *አንቀጽ 39. ኢትዮጵያዊ ስደተኞችን በተመለከተ*

39.1. በመላው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያዊ ስደተኞችን ደህንነት መከታተል
39.2. በመላው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያዊ ስደተኞች ወደ ሀገር በመመለስ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን እንዲያገለግሉ ማመቻቸት
39.3. በውጭው ዓለም ካሉ የኢትዮጵያን ኮሚኒቲና ማኅበረሰቦች ጋር ቀና ግንኙነት መፍጠር

## *የሀገር መከላከያና ደህንነት*

### *አንቀጽ 40. የመከላከያ ኃይል*

40.1. ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣና ተጠሪነቱም ለምክር ቤቱ የሆነ የሀገር መከላከያ ጦር ሠራዊት መገንባት
40.2. ከክፍለሀገር እስከ ወረዳና ቀበሌ የተዋቀረ የፖሊስ ሠራዊት መገንባት
40.3. የጦር ሆነ የፖሊስ ሠራዊቱ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ተጽዕኖ ነፃ ይሆናሉ
40.4. የጦር ሆነ የፖሊስ ሠራዊቱ አባላት የፖለቲካ ድርጅት አባል አይሆኑም
40.5. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወታደራዊ ክንፍ ወይም ሠራዊት አይኖረውም
40.6. ለሠራዊቱ አባላትና ለቤተሰቦቻቸው የሚገባውን ደህንነትና ጥንቃቄ ማድረግ
40.7. በግዳጅ ተሠማርተው ለተሰዉ ወይም አካላቸው ለተጎዳ የሠራዊቱ አባላትና ቤተሰቦች በትምህርት፣ በጤና እና በሌሎች መስኮች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
40.8. የሠራዊቱ አባላትን የጡረታ መብታቸውን ማስከበር
40.9. በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 36.2. እንደተጠበቀ ከውጭ ኃይሎች ወታደራዊ ጥገኝነት አለመመሥረት

# ሕዝባዊ ጥሪ

ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን በአለው የወያኔ አገዛዝ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰች ነው። ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ተዳክማና ተከፋፍላ እንዳሻቸው ሊገዟትና አንጡራ ሀብቷን ለመዝረፍ ዕቅዳቸው የሆነ የውጭ ኃይሎችና የሀገር ውስጥ አምባገነኖች ዛሬ በወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ መሪነት ሀገሪቷ ልትበታተን እምትችልበት አደገኛ ሁኔታ ላይ እየገፏት ይታያል።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ስለ ሰንደቅ ዓላማዋ ክብር፣ ስለ ጥንታዊት ሀገርነቷ ተረት ተረት የሆነበት ወያኔ ዛሬ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል። “ወያኔ ያልገዛት ኢትዮጵያ ትበታተናለች” ያለውን ተግባራዊ ለማድረግ በረጨው የዘር ማጥፋት ተግባሩ በሰፊው ተያይዞታል። በኦሮሞ ተወላጆች ላይ በተለያዩ ግዛቶች በቅርቡ ያደረሰውና እያደረሰ ያለው ጭፍጨፋ፣ እሥርና እንግልት እጅጉን አስከፊ ነው። ገና ከጅምሩ አማራው ላይ ያነጣጠረው የዘር ማጥፋት ተግባሩ ዛሬ አድማሱን እያሰፋና ይፋ እየወጣ ይታያል።

ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ ከሥልጣኑና ከንዋይ የዘለለ ሀገርና ሕዝብ አያሳስቡትምና ሀገር ሊያጠፋ የተከመረ አሸባሪ ቡድን ነው። የዓለም መንግስታት አውቀውም ይሁን ተታለው በመንግሥት ደረጃ ያለ ኢትዮጵያዊ አሸባሪ ኃይል ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ መሆኑን እራሱ እንደሚመሰክርላቸው ቀናት እየቀረቡ ነው። አዎ ሕዝባችን ከአለበት አሰቃቂ የኑሮ ደረጃ በወረደና በዘቀጠ መልኩ ከትርፍራፊና ከጉርሻ አልፎ ከጥራጊ ቆሻሻ እንዲበላ የተገደደበት ዘመነ መርግምት ቢኖር የወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ ነው። ሕዝባችን በመንደርና በሠፈርተኝነት የመሠረተው ፍቅርና አብሮ የመኖር ባህል ተበጣጥሶ ግለኝነት ይበራከት ዘንድ ከቀዬውና መኖሪያውን እየጣለ እንዲፈናቀልና እንዲወረወር የተደረገው የስቃይ ዘመን በወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ ነው። ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ የፈጠረው የዘር ፖለቲካ በሀገራችን የእርስ በርስ ጦርነት እንዲቀሰቅስና አንዱ ዘር በሌላ ወገኑ ይነሳ ዘንድ የተሸረበው ሀገር የማጥፋት ትልዕኮ ሁሉም ዜጋ እንዲያጤነውና እንዲገነዘበው ያስፈልጋል። ይህንን ከፋፋይና በታኝ አገዛዝ ወደ ከርሰ መቃብሩ በመክተት ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ትቀጥል ዘንድ ኃላፊነት ያለብን ዜጎቿ በሙሉ በጋራ ለጋራ ትግል ልንነሳሳ ግድ ይለናል። ቅድሚያ ሀገራችን ናትና ኢትዮጵያን እናድናት እንላለን። ቅድሚያ ሕዝባችን ነውና በኑሮ ጅራፍ የተገረፈው ሕዝባችን በጥይት እየተቆላ ነውና እንድረስለት። ለአዛውንት እናቶችና አባቶች እግዝዮታ ልንደርስላቸው ይገባናል። የሕፃናት ልቅሶ ሊሰማን ይገባል። የወጣቶች መቀጥቀጥ ሊያመን ይገባል። ለሀገራችንና ለሕዝባችን ህልውና ዋንውን ፍልሚያ ማገዝ፣ መደገፍ ኢትዮጵያዊ ግዴታችን መሆን ይገባዋል። ዛሬ ኢትዮጵያን ልናድን የምንችለው ዋናውን ትኩረታችን በሀገራችን የአንድነት ፀር በሆነው ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግና በአጋሩ ሻቢያ ላይ አድርገን መሆኑን ልናሰምርበት እንወዳለን።

በመሆኑም ዘረኛውን ወያኔ/ህወሀት/ኢ.ሕአዴግ ለማስወገድና በቀጣይነትም የሀገራችንን እና የሕዝባችንን አንድነት ባስጠበቀ መልኩ “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር” ነገም እምነታችን እንዲሆን ትግሉን በጋራ መርተን በጋራ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ እንወስን ዘንድ ጥሪያችንን፦

- ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ
- ለሁሉም በሀገር ውስጥ ከሀገር ውጭ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች
- ለኢትዮጵያን የሙያና የብዙሃን ድርጅቶች በሙሉ
- በኢትዮጵያ ለሰባዊ መብት ተሟጋች ኃይሎች
- ለሴቶች እህቶቻችን፣ ለወጣቶች፣ ለተማሪዎች፣ ለታዳጊ ሕፃናት
- ለተለያዩ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተቋማትና አድባራት
- ለአዛውንት እናትና አባቶች

- በሀገር ቤትም ከሀገር ውጭ በተለያዩ የሀገራችን ቋንቋ ለሚተላለፉ የሬድዮና ቴሌቪዥን ዝግጅት ክፍሎች
- በሀገር ቤትም ከሀገር ውጭ ላሉ ኢትዮጵያዊ ድረ ገጽ ክፍሎች
- በሀገር ቤትም ከሀገር ውጭ ላሉ ኢትዮጵያዊ የፓልቶክ መወያያ ክፍሎች
- በወያኔ የመንግሥት እርከን ተካፋይ ለሆናችሁ ተለጣፊ የፖለቲካ ድርጅቶች
- በወያኔ ጥላ ሥር ለተሰለፋችሁ የሠራዊቱ አካላት

በ"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ስም ኢትዮጵያዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!**

**እግዚሃብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**

**መስከረም 08 ቀን 2009 ዓ.ም. (September 18, 2016)**

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com